



ገጽ 4

ቦርሳ ውስጥ የተገኙ 20 ወፎች

ገጽ 5



በሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተው የነበሩ 149 ግብር ከፋዮች

ገጽ 6


# ገቢያችን ህልውናችን

14ኛ ዓመት | ቁጥር 162 | ሚያዝያ 2015 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል


## በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴ ግብር ከፋዮች ከ61 ቢሊዮን ብር በላይ ከፍለዋል

ወ/ሮ ባለፉት አስር ወራት በኤሌክትሮኒክ የመክፈያ ዘዴ ግብራቸውን ከከፈሉ 20ሺ 772 ግብር ከፋዮች 61 ቢሊዮን 468 ሚሊዮን 847ሺ 530 ብር መሰብሰቡን በገቢዎች ሚኒስቴር የገቢ ሂሳቦች ዳይሬክቶሬት ገቢ ሂሳቦች ማጠቃለያ ቡድን አስተባባሪ ገለጹ፡፡

አስተባባሪዋ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አሸናፊ እንደገለፁት ከነዚህ ግብር ከፋዮች ውስጥ 8ሺ 56ቱ በያዝነው የበጀት ዓመት የክፍያ አማራጩን ለመጠቀም የተመዘገቡ ናቸው፡፡

ሥርዓቱ ግብር ከፋዮች ከበርካታ የገንዘብና የጊዜ ብክነት ተላቀው በቀላሉ ግዴታቸውን እንዲወጡ ያስቻለ መሆኑንም ቡድን አስተባባሪዋ ጠቁመዋል፡፡

የኤሌክትሮኒክ መክፈያ ሥርዓት ከተዘረጋበት ጊዜ አንስቶ 22ሺ 419 ግብር ከፋዮች 127 ቢሊዮን 180 ሚሊዮን 14ሺ 279 ብር የከፈሉ መሆናቸውን ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አስታውሰዋል፡፡



## ኮሚሽኑ የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ስምምነትን ተፈራረመ

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እና ከኢትዮጵያ ብዙኃን መገናኛ ባለስልጣን ጋር የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራርሟል፡፡

በፊርማ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ እንደተናገሩት፤ የጉምሩክ አሠራርን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑም ጠቁመው ወደዚህ ሥርዓት እየገቡ ያሉ ተቋማት ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ ለደንበኞች ተደራሽነት ያለው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው ብለዋል፡፡

ኮሚሽኑ ... ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ዘጠኝ የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደሮች ተሾሙ



የገቢዎች እና የጉምሩክ አመራሮች አዲስ ከተሾሙት እና ከተሸኙት ከፊል የታክስ እና ጉምሩክ አምባሳደሮች ጋር፤



በክብር ከተሸኙት የታክስ አምባሳደሮች መካከል መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ ይገኙበታል፤

የገቢዎች ሚኒስቴር ከ2011 ዓ.ም. ጀምሮ በታክስ አምባሳደርነት ሲያገለግሉ የነበሩትን 10 ታዋቂ ሰዎች በክብር በማሰናበት ሌሎች ዘጠኝ የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደሮችን ሾሟል፡፡

አዲስ የተሾሙት አምባሳደሮች የሀገርን ገጽታ በመገንባት፣ የማህበረሰብን አስተሳሰብ በበጎ በመቅረጽ እና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ናቸው፡፡

የቀድሞዎቹን አምባሳደሮች በምስጋና በመሸኘት አዳዲሶቹን የሾሙት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፤ አዲስ የተሾሙት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

አዲስ የተሰየሙት የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደሮች

1. አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ
2. አቶ ግርማ ገ/ጻድቅ
3. ሊቀ ትጉኃን ታጋይ ታደለ
4. አቶ ቢኒያም በለጠ
5. ወ/ሮ ሀናን መሀመድ
6. ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ
7. ዶ/ር ማሙሽ ፈንታ
8. ዶ/ር ወዳጄነህ መሀረነ እና
9. ዶ/ር ምህረት ደበበ ናቸው፡፡

በክብር የተሸኙት የታክስ አምባሳደሮች

1. ደራሲ ጌታቸው በለጠ
2. አርቲስት አረጋኸኝ ወራሽ
3. አርቲስት ሐመልማል አባተ
4. መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ
5. ሙኃዘ-ጥበባት ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
6. ኡስታዝ አቡበከር አህመድ
7. አምባሳደር ሀሰን ታጁ
8. አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ
9. ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ እና
10. አምባሰደር ሙሉ ሰሎሞን ናቸው፡፡

# ርዕሰ አንቀጽ

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አዲሱ ይርጋ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጅ፡- በኃይሉ ሽመልስ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 011-6-62-98-17 ፋክስ 011-6-67-39-14
ፖ.ሣ.ቁ 2559 ዌብሳይት www.mor.gov.et
ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia
ለታክስ እና ለጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ 8199



## አምባሳደሮቻችን

ይህ ቃል በብዛት የሚታወቀው አንድን ሀገር ወክለው በሁሉም ዘርፍ የወከላቸውን ሀገር ፍላጎት ከተወከሉባቸው ሀገራት ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ ከሚሠራው ሥራ ጋር ነው፡፡ በዚህም የየሀገራቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ፍላጎቶች በየመንግሥቶቻቸው በተወከሉ አምባሳደሮች አማካኝነት የሚከናወኑ ሲሆን ቅድሚያ የሚሰጠው የሀገርን ጥቅም በማስቀደም መርህ ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡

ይህ ስያሜ ከላይ ከተገለጸው ተግባር ሌላ በተቋማትም ተሰይሞ አንድ ተቋም ዓላማ ለማራመድ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በዚህ መሠረት የገቢዎች ሚኒስቴርም የተቋቋመለትን ዓላማ በተሳካ ሁኔታ ለማራመድ «የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደር» በማለት በተሰማሩባቸው የተለያዩ መስኮች ታዋቂ የሆኑትንም ሆነ ውጤታማ ሥራ የሠሩትን ሰዎች ከ2011 ዓ.ም. ጀምሮ መሾም ጀምሯል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2011 ዓ.ም. 10 የታክስ አምባሳደሮችን የሾመው ከኪነ-ጥበቡ፣ ከስፖርቱ፣ ከሃይማኖት ድርጅቶች እና ከማኅበራት ሲሆን ግለሰቦቹ በኅብረተሰቡ ውስጥ በነበራቸው በጎ ተግባር ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው የጎላ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት አምስት ዓመታት በዋናነት ለግብር ከፋዮች አነቃቂ እና አነሳሽ የግብር መልዕክቶችን ሲያስተላልፉ የቆዩ ሲሆን በሌሎች የሚኒስቴሩ ተግባራትም ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ሲሳተፉ ቆይተዋል፡፡

ዘንድሮ ደግሞ ነባሮቹን በክብር በማሰናበት ዘጠኝ አምባሳደሮችን የመሾም ሥነ-ሥርዓት የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮች እና ሠራተኞች በታደሙበት ተካሒዷል፡፡ ይህ ሹመት ውክልናውን ከባለፈው ሰፋ አድርጎ ስፖርተኞችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ የበጎ አድራጎት ተቋማትን፣ አነቃቂ ንግግር አዋቂዎችን፣ እና የቀድሞው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባልደረቦችን ያካተተ ሆኗል፡፡

እነዚህ አምባሳደሮች የተመረጡት ታዋቂ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በተሰለፉበት መስክ ባሳዩዋቸው ውጤታማ ተግባር በኅብረተ-ሰቡም ዘንድ ተሰሚነት ስላላቸው ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ተገንዝበው እና ምንም እንኳን የተጣበበ ጊዜ እንዳላቸው ቢታወቅም ሀገርን ለመጥቀም ከዚህ በላይ አደራ የለምና በሚችሉት ልክ ግብር ከፋዮችንም ሆነ ሌላውን የኅብረተ-ሰብ ክፍል የሕግ ተገዢነታቸው እንዲጨምር የማሳመን ተግባራቸውን እንዲወጡ እንጠይቃለን፡፡

የገቢው ዘርፍ ተቋማት በበኩላቸው፤ በተለያዩ መስፈርቶች ተመዝነው የተመረጡት የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደሮች የተሾሙበትን ዓላማ ለማራመድ ሙሉ ፈቃዳቸውን ስለገለጹ የገቢ ዕቅዳችን የተሳካ እንዲሆን በምታደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ በመጋበዝ ለግብር ከፋዮችም ሆነ ለሠራተኞች እን ለአመራሮች አነሳሽ መልዕክታችውን እንዲያስተላልፉ፤ በሌሎች ተግባራት ላይም እንዲሳተፉ እንድታደርጓቸው እናሳስባለን፡፡

ይህን ማሳሰብ ያስፈለገው የገቢው ዘርፍ ዕቅድ የሚሳካው በተለመደው መልኩ ስለግብር ከፋዮች መብት እና ግዴታ በማስተማር፣ በመቀስቀስ እና ከሕግ ውጪ የሆኑት ላይ የሕግ እርምጃ በመውሰድ ብቻ ሳይሆን በእንዲህ ዓይነት መልኩ የማሳመን ተግባርም በማከናወን ስለሆነ ነውና ሁሉም የየድርሻውን እንዲወጣ እናስገነዝባለን፡፡




## የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያን በቴሌ ብር ተጀመረ

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በቴሌ ብር ለመክፈል የሚያስችል የማስጀመሪያ ሥነ-ሥርዓት እና ስምምነት በጉምሩክ ኮሚሽን እና በኢትዮቴሌኮም መካካል ተፈጽሟል፡፡

ሥነ-ሥርዓቱ የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ እና የኢትዮቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሪት ፍሬሕይወት ታምሩ በተገኙበት ተከናውኗል፡፡

ኮሚሽነሩ፤ የገቢ እና የወጭ ንግዱ የተቀላጠፈ እንዲሆን እና በአገልግሎት አሰጣጥ የሚታዩ መንገላታቶች እንዲቀንሱ መደረጉን ገልጸው በወረቀት አልባ ዘመን ክፍያን በቴሌ ብር ማከናወን የአገልግሎት አሰጣጥን ተደራሽ ለማደረግ ሚናው የጎላ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ድርጅታቸው ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማደረግ እየሠራ መሆኑን ተናግረው ከኮሚሽኑ ጋር የተደረገው ስምምነት በቴሌ ብር አማካይነት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በፍጥነት እና በየትኛውም ቦታ ያለምንም እንግልት እንዲከፈል እንደሚሠሩ አስታውቀዋል፡፡

## የታክስ አስተዳደሩን ለማዘመን የአለም ባንክ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገለጸ

የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር ሥርዓት፣ በቴክኖሎጂ እና በሰው ሀብት አስተዳደር ተግባራት ላይ ከዓለም ባንክ ልዑካን ጋር ተወያይቷል፡፡

በውይይቱ ላይ የገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ስርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ቱሉ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ የተለያዩ ልማቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኘው የዓለም ባንክ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን ለማዘመንና በሰው ሀብት አስተዳደር ላይ እየሠራቸው ላሉት ተግባራት ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡ ሀገር በቀል ኢኮኖሚን ለማሳደግ ሀገራችን የአስር ዓመት መሪ እቅድ አውጥታ እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ ጠቁመው ሚኒስቴሩም የራሱን የአስር ዓመታት መሪ ዕቅድ በማዘጋጀትና የሚሰበሰበውን ገቢ በማሳደግ ላይ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

የዓለም ባንክ ተወካይ ሚስተር ማኑኤል ቫርጋስ፤ ኢትዮጵያ በገቢው ዘርፍ እያሳየች ያለው ለውጥ አበረታች እና ተስፋ ሰጪ መሆኑን በቆይታቸው መገንዘባቸውን ገልጸው ይህንኑ ዓላማ ለማሳደግ አስፈላጊውን የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ መሰረት መስቀሌን ጨምሮ ሌሎች የሚኒስቴሩ እና የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡






ሚኒስትሯ እና የኢቢሲ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የስምምነት ሰነዱን ሲፈራረሙ፤



ሚኒስትሯ ከፊርማ ሥነ-ስርዓቱ አስከትለው የኢቢሲ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጋር ጉብኝት ሲያደርጉ፤

# ሚኒስቴሩ እና ኮርፖሬሽኑ በጋራ ለመሥራት ተፈራረሙ

የገቢዎች ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን (ኢ.ቢ.ሲ) በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የስምምነት ሰነድ ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱን የፈረሙት የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፍስሃ ይታገሱ ናቸው፡፡

በስምምነቱ ላይ ሚኒስትሯ እንደገለጹት «ግብር፤ ለሀገር ክብር» በሚል የተጀመረው ሀገራዊ ንቅናቄ እነዲሳካ እና ሀገራዊ ወጪን በራስ ገቢ ለመሸፈን የተያዘውን ራእይ እውን እንዲሆን የኢ.ቢ.ሲ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በለውጥ ላይ የሚገኘው ኢ.ቢ.ሲ የማህበረሰቡን የታክስ ግንዛቤ ለማሳደግ በጋራ ሲሠራቸው የነበሩትን ሥራዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ በቅንጅት እና በጥሩ አቀራረብ ለመስራት ያስችላል ብለዋል፡፡

የኢ.ቢ.ሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍስሐ ይታገሱ በበኩላቸው፤ ግብር በሚፈለገው ልክ እንዲሰበሰብ የሚያስችለው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ዋነኛ ተልእኳችን ነው ብለው ከሚኒስቴሩ ጋር በትብብር እየተሠሩ ያሉትን ፕሮግራሞች በአዲስ ይዘት እና አቀራረብ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በእለቱ በሸጎሌ እየተገነባ ያለውንና የሥራ መንፈስን እንዲያነሳሳ ደርጎ የተሠራውን የኢ.ቢ.ሲ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ እና ግቢ የሁለቱም ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እና የሚኒስቴሩ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ሠራተኞች ጎብኝተዋል፡፡

# በሞባይል ...

ከገጽ 5 የዞረ

መገናኛ ብዙሀን ላይ ድጋፍ ለማግኘት ባቀረቡት የድጋፍ ጥሪ መሰረት ከ1500 ዶላር በላይ ለመሰብሰብ ችለው ነበር።

ሳይንቲስቶቹ እዳ ውስጥ የከተታቸው ንሥሮቹ የት እንዳሉ በሚያመለከተው አጭር መልዕክት አማካይነት አእዋፋቱ ለደህንነታቸው አመቺ የሆነ ስፍራ መድረስ አለመድረሳቸውን በሳይንሳዊ መንገድ ለማወቅ ያስችላቸዋል።

ለየት ያለ የንሥር ዝርያ እንደሆኑ ከሚነገርላቸው ሚን ከተባሉት ንሥሮች መካከል አጥኚዎቹ 13ቱን በአሁኑ ጊዜ የት እንዳሉና ያሉበትን ሁኔታ እየተከታተሉ ሲሆን በዚህ ወቅት ከሚራቡበት የሳይቤሪያና የካዛኪስታን አካባቢዎች ወደ ደቡብ እስያ ይሄዳሉ።

የሞባይል ስልክ አገልግሎት አቅራቢው ሜጋፎን፤ የሳይንቲስቶቹን እዳ መሰረዙ የጀመሩትን ንሥሮቹን የመከታተል ሥራ እንዲቀጥሉ ከማስቻሉ በተጨማሪ ለደህንነታቸው የሚያስፈልግ በጣም ጠቃሚ መረጃን ለመሰብሰብ ያግዛል ተብሏል።

# ምግብን እንደ...

ከገጽ 5 የዞረ

## 4. ቃርያ

- ቫይታሚን ኤ ዋነኛ ከሚባሉ ቃርያ ውስጥ ከሚገኙ ንጥረ-ነገሮች የሚገኝ ስለሆነ ለዓይን ጥራት እና ጤናማነት ከፍተኛ ሚና አለው፤
- በቫይታሚን ሲ እጅግ የበለጸገ በመሆኑ ቆዳችንን ጤናማና የሚያበራ እንዲሆን ያደርጋል፤
- በሽታን የመከላከል አቅምን ያዳብራል፤
- የምግብ መፈጨት ሂደትን ያፋጥናል-
- ጉንፋን፣ ሳል እና የሳንባ ካንሰርን ይከላከላል፤
- ለአጥንት ጤናማነት እና ጥንካሬ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን ለሰውነታችን ጠቃሚ ያልሆኑ ንጥረ-ነገሮችን በማስወገድ እና የፋይበር ምንጭ በመሆን የሆድ ድርቀትን ይከላከላል፤
- ቃርያን የሚመገቡ ሰዎች የቆዳ መሸብሸብ እንዳይኖራቸው እንዲሁም ቶሎ እንዳያረጁ ያደርጋል።

## 5. አቮካዶ

- በሰውነታችን የሚገኝን የኮሌስትሮል መጠን ዝቅ ያደርገዋል፤
- በውስጡ ያዘለው ቫይታሚን ኤ ለልብ ህመም ወይም ለስትሮክ የመጋለጥ ዕድልን በእጅጉ ይቀንሳል፤
- እርጅናን ለመከላከል እና የቆዳ ውበት ተጠብቆ እንዲቆይ ይረዳል፤
- በአቮካዶ ውስጥ በብዙ መጠን የሚገኘው አንቲ ኦክሲዳንት ቆዳ እንዳይሸበሸብ እና የሞቱ የቆዳ ሴሎች እራሳቸውን እንዲተኩ ሲያግዝ ካሮቲኖይድስ የተባለው ንጥረ ነገርም በቆዳ ላይ የሚታዩና የቆዳን ውበት የሚቀንሱ ምልክቶችን እንዳይከሰቱ ያደርጋል፤
- ክብደት ለመቀነስ ይረዳል፤
- በአቮካዶ ውስጥ በጥሩ መጠን የሚገኘው ፖታሺየም በደማችን ውስጥ ያለውን የጉልኮስ መጠን በማመጣጠን በሰውነት ውስጥ የልብ ሥራን እና የስኳር መጠንን የተረጋጋ እንዲሆን ያስችላል።

## 6. ቀይ ሽንኩርት

- የሰውነትን ከበሽታ የመከላከል አቅም ያሳድጋል፤
- ክሩሚየም የተሰኘው ንጥረ-ነገሩ የደም ግፊትንና ስኳርን ይቆጣጠራል፤
- ገላን የማሳከክና የማቃጠል አይነት ባህሪ ያላቸውን አለርጂዎች ይቆጣጠራል፤
- ጥሬውን መመገብ ኮሌስትሮልን ከመቆጣጠሩ ባሻገር የጤናማ ልብ ባለቤት ያደርጋል፤
- ክዩርስቲን የተባለው በቀይ ሽንኩርት ውስጥ የምናገኘው ንጥረ-ነገር ካንሰርን የመከላከል ሚና አለው፤
- በንብ የተነደፈ ሰው በቀይ ሽንኩርት ውሃ ቢቀባ ከስቃዩ እፎይታን ያገኛል፤
- ቀይ ሽንኩርትን በየእለቱ መጠቀም ከጨጓራ አልሰር ይጠብቃል፤
- አረንጓዴ ጫፍ ያለው ለጋ ቀይ ሽንኩርት የቫይታሚን ኤ ይዘቱ ከፍተኛ በመሆኑ ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ አለው።

## 7. ድንች

- ለጨጓራ ህመም ፈውስ ይሰጣል፤
- ለደም ግፊት ፍቱን መድሐኒት ነው፤
- ለካንሰር፣ ለኩላሊት፣ ለራስ ምታት እና ለሌሎችም መድሐኒት ነው፤
- የድንች ጭማቂ የተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅምን ያሻሽላል፤
- በየጊዜው የሚከሰት የራስ ምታት ህመምን እና የወር አበባን ተከትሎ የሚከሰቱ ህመሞችን ለማስታገስ ይረዳል፡፡

ከገጽ 4 የዞረ

- በወር የ1ሺ. 500 ብር ቤት አከራይ በዓመት 18ሺ. ብር ያገኛል፡፡ ይህ ገቢው ተራ ቁጥር 2 ላይ የሚያሳርፈው ሲሆን ስሌቱ፡-

ግብር የሚከፈልበት ገቢ = (የዓመት ገቢው x የትርፍ መተመኛ መቶኛ)

ግብር የሚከፈልበት ገቢ = 18,000 x 50%

ግብር የሚከፈልበት ገቢ = 9,000

ዓመታዊ ግብሩ = (9,000 x 10% - 720)

ዓመታዊ ግብሩ = 180

ይህ የሚሰራው ግብርን በግምት ለሚከፍሉ (የሒሳብ መዝገብ ለመያዝ ለማይገደዱት) አከራዮች ሲሆን የትርፍ መተመኛ መቶኛው (50%) በክልሎች በኩል የተለየ የትርፍ መተመኛ መቶኛ ጥቅም ላይ እስካልዋለ ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በወጥነት ተግባራዊ የሚሆን ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ ‹‹ሐ›› ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ

| የንግድ ስራ ገቢ በዓመት | የግብር ማስከፈያ መጣኔ | ተቀናሽ ብር |
|---|---|---|
| ከብር 0-1,800 | 0% | 0 |
| ›› 1,801-7,800 | 10% | 180 |
| ›› 7,801-16,800 | 15% | 570 |
| ›› 16,801-28,200 | 20% | 1,410 |
| ›› 28,201-42,600 | 25% | 2,820 |
| ›› 42,601-60,600 | 30% | 4,950 |
| ከ ›› 60,600 በላይ | 35% | 7,950 |

ለምሳሌ፡- ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ለመደበኛ ቁርጥ ግብር አወሳሰን በሚያገለግለው የትርፍ መተመኛ መቶኛ ሰንጠረዥ መሰረት አንድ በሸቀጣ ሸቀጥ የንግድ ዘርፍ የተሰማራ ነጋዴ የንግድ ሥራ ገቢው በዓመት 80ሺ. ብር ቢሆን የዘርፉ አማካይ የትርፍ መተመኛ መቶኛ = 14%

ግብር የሚከፈልበት ገቢ (80,000 x 14%) = 11,200

ዓመታዊ ግብሩ = ግብር የሚከፈልበት ገቢ x የግብር ማስከፈያ መጣኔ - ተቀናሽ ብር

ዓመታዊ ግብሩ = 11,200 x 10% - 720

ዓመታዊ ግብሩ = 400

ይህ የሚሰራው ግብርን በግምት ለሚከፍሉ (የሒሳብ መዝገብ ለመያዝ ለማይገደዱት) ሲሆን የሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ ለሚገደዱት ግን ወደ ማስከፈያው መጣኔ ከመደረሱ በፊት ግብር ከፋዮች ወጪዎቹን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ሥራው ገቢ ለማግኘት፣ ለንግድ ሥራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡

ለግንዛቤዎ

# ክሊራንስ ለመስጠት ኦዲት የማያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች ታክስ ከፋዩን ኦዲት ማድረግ ሳያስፈልግ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል:-

1. ንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የሙያ ፍቃድ ለማደስ፤
2. ጨረታ ለመካፈል ወይም ለመሳተፍ፤
3. ለተሽከርካሪዎች ወይም ለኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ (ክላውዶ) ለማድረግ፤
4. የባንክ ብድር ለማግኘት፤
5. የመድን ካሳ ለማግኘትና የተሽከርካሪ ሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፤
6. የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፤
7. የንግድ ሥራ ሀብት መቀነስን ሳይጨምር የንግድ ዘርፍ ቅነሳ ለማድረግ፤
8. ድርጅቶች እንደገና ተደራጅተው ሲዋሀዱ የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳ አካቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የፀደቀ ሰነድ ለማቅረብ፤

የክሊራንስ ጥያቄ በቀረበበት ጊዜ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የተሰጠው እና ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት ታክስ ከፋይ ኦዲት ሳይደረግ የባንክ ብድር እንዲወስድ ክሊራንስ የሚሰጠው ዕዳውን የከፈለ እንደሆነ ወይም ለመክፈል የባንክ ዋስትና ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡




ታክስ ከፋዩ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ሊሰጠው የሚችለው:-

1. ታክስ ከፋዩ ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቂያ እና መክፈያ የመጨረሻ ቀን ከመድረሱ በፊት የንግድ ሥራ ፍቃድ ለማደስ፣ በጨረታ ለመሳተፍ፣ የባንክ ብድር ለመውሰድ እና የጉዳት ካሳ ለማግኘት የሚቀርብ የታክስ ክራንስ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ከሆነ ጥያቄው ከቀረበበት የግብር ዘመን በፊት ታክሱን አስታውቆ ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ እና

2. የታክስ ክራንስ ምስክር ወረቀት የተጠየቀበትን አገልግሎት ዓይነትና የተፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

የባንክ ብድር ለማግኘት የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለጠየቀ ሰው የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ጥያቄ አቅራቢው የንግድ ሥራ ያልሠራና በግብር ከፋይነት ያልተመዘገበ ከሆነ ከታክስ መሥሪያ ቤቱ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከመረጃ ቋት ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ጠያቂው በንግድ ሥራ አለመሠማራቱን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

የንግድ ሥራ ፍቃድ ለመመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከታክስ ሚኒስቴሩ የሥራ ክፍሎች እና ከሦስተኛ ወገን በማጣራት የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚገቡ እቃዎች

የገንዘብ ሚኒስቴር የግል መገልገያ እቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር የሚገቡበትን እና የሚወጡበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ መመሪያውም ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ከሀገር የሚወጡ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014 በመባል ይታወቃል፡፡ በዚሁ መመሪያ መሰረት ለግል መገልገያ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆነው የሚገቡ እቃዎች የሚከተሉት ናቸው:-

ማንኛውም መንገደኛ የሚከተሉትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ለግል መገልገያነት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፤

| ተ.ቁ. | የዕቃ ዝርዝር | መለኪያ | የሚፈቀደው መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | ሲጋራ | ግራም | 200 |
| 2 | ሲጋር | በቁጥር | 20 |
| 3 | ብትን ትንባሆ | ግራም | 250 |
| 4 | የአልኮል መጠጥ | ሊትር | 2 |
| 5 | ለስላሳ ሽቶ | ሚሊ. ሊትር | 500 |
| 6 | ሽቶ | ሚሊ. ሊትር | 500 |
| 7 | ሞባይል | በቁጥር | 2 |
| 8 | ላፕቶፕ | በቁጥር | 1 |
| 9 | የፎቶ ግራፍ ካሜራ | በቁጥር | 1 |
| 10 | ዊልቸር | በቁጥር | 1 |
| 11 | የእጅ ሳዓት | በቁጥር | 1 |
| 12 | የጺም ወይም የጸጉር መላጫ | በቁጥር | 1 |
| 13 | የጸጉር ማድረቂያ | በቁጥር | 1 |
| 14 | የጸጉር መተኮሻ | በቁጥር | 1 |
| 15. | መንገደኛው የሚጠቀምባቸው መድሃኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች | በቁጥር | ለአንድ ሰው በሚያስፈልግ መጠን |
| 16. | በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለቤተሰብ የሚያገለግሉ፣ልብሶች፣ጫማዎች እና የጽዳት እቃዎች | በቁጥር | ለአንድ ቤተሰብ ከሚያስፈልገው ያልበለጠ |

| የመቀጠር ገቢ በወር | የግብር ማስከፈያ መጣኔ | ተቀናሽ ብር |
|---|---|---|
| ከብር 0-600 | 0% | 0 |
| » 601-1,650 | 10% | 180 |
| » 7,801-16,800 | 15% | 570 |
| » 16,801-28,200 | 20% | 1,410 |
| » 28,201-42,600 | 25% | 2,820 |
| » 42,601-60,600 | 30% | 4,950 |
| ከ » 60,600 በላይ | 35% | 7,950 |

### የግብር ማስከፈያ መጣኔዎች

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 መሠረት አምስት ዓይነት የገቢ ሠንጠረዦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም:-

1ኛ:- ሠንጠረዥ «ሀ» ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤
2ኛ:- ሠንጠረዥ «ለ» ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፤
3ኛ:- ሠንጠረዥ «ሐ» ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ፤
4ኛ:- ሠንጠረዥ «መ» ከሌሎች ገቢዎች፤
5ኛ:- ሠንጠረዥ «ሠ» ከግብር ነጻ የሆኑ ገቢዎች፤

**ሠንጠረዥ €€ሀ« ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤**

**ሴ:- የ4ሺ 500 ብር ተቀጣሪ ግብር ተቀንሶበት የተጣራ ደመወዙ ይህ ነው::**

ይህ ደመወዝ ተራ ቁጥር 4 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ስሌቱ:-
ተቀናሽ ግብር = የወር ደመወዝ x የማስከፈያ መጣኔ - ተቀናሽ ብር
ተቀናሽ ግብር = 4,500 x 20% - 302.50
ተቀናሽ ግብር = 597.50
የተጣራ ደመወዝ = አጠቃላይ ደመወዝ - ተቀናሽ ግብር
የተጣራ ደመወዝ = 4,500 - 597.50
የተጣራ ደመወዝ = 3ሺ 902 ብር ከ50 ሳንቲም (ይህ የጡረታ ተቀናሽን አያካትትም)

**ሠንጠረዥ«ለ» ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ**

| ተ.ቁ. | የቤት ኪራይ ገቢ በዓመት | የግብር ማስከፈያ መጣኔ | ተቀናሽ ብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ከብር 0-7,200 | 0% | 0 |
| 2 | » 7201-19,800 | 10% | 720 |
| 3 | » 19,801-38,400 | 15% | 1,710 |
| 4 | » 38,401-63,000 | 20% | 3,630 |
| 5 | » 63,001-93,600 | 25% | 6,780 |
| 6 | » 93,601-130,800 | 30% | 11,460 |
| 7 | ከ » 130,001 በላይ | 35% | 18,000 |

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



# በየዓይነቱ

አዘጋጅ፡- በኃይሉ ሺመልስ

# ምግብን እንደ መድሐኒት

ምግባችንን እንደመድሐኒት ካልወሰድን መድሐኒትን እንደ ምግብ የምንወስድበት ጊዜ ይመጣልና እነዚህን በመውሰድ ምግባችን መድሐኒት እናድርገው፡፡

## 1. ፓፓያ

- የሞቱ የቆዳ ሴሎችን ለማስወገድ ይረዳል፤
- የቆዳ ድርቀትን ይከላከላል፤
- ቆዳን በመቀባት ወይም በመመገብ የሚያምር ለስላሳ ቆዳን መጎናፀፍ ይቻላል፤
- የተፈጨ ፓፓያ የተሰነጣጠቀ ተረከዝን ለማከም ይጠቅማል፤
- የሞቱ ሴሎችን ከቆዳ ላይ ማስወገጃ ተፈጥሮአዊ መንገድ ነው፤
- የቆዳን ተፈጥሯዊ ቀለም ለመመለስ ይረዳል፤
- ለሆድ ትላትል ህክምናነት ይጠቅማል፤
- ጥቁር ነጠብጣቦችን ለማስወገድ በቆዳ ላይ የሚታዩ የእርጅና ምልክቶችን ለመቀነስና ለማከም ይረዳል፤
- ራሰ በራነትን ይከላከላል፤
- የፀጉር እድገትንና ጥንካሬን ይጨምራል።

## 2. ሎሚ

- ጸረ-ባክቴሪያ ባህሪ አለው፤
- በቫይታሚን ሲ የበለጸገ ነው፤
- የሎሚ ጭማቂ በውሃ ቀላቅሎ መጠጣት ሰውነታችን የአሲድ አልካላይን ሚዛኑን ለመጠበቅ ይረዳዋል፤
- የጉበትን ሽራ በማነቃቃት ዩሪክ አሲድንና ሌሎችንም ጎጂ ንጥረ-ነገሮች ከሰውነታችን ውስጥ ለማስወገድና የሀሞት ፈሳሽንም የፈሳሽነት ባህሪውን እንዳያጣ ያደርጋል፤
- የሎሚ ጭማቂ በቫይታሚን ፒ የበለጸገ እንደመሆኑ ከህዋሳት መጎዳትና በእድሜ መጨመር ሳቢያ የሚከሰቱትን ‘ፍሪ ራዲካሎችን ለማስወገድ ይረዳል፤
- የሎሚ ጭማቂ ጸረ-ካንሰር ባህሪያት አሉት፤
- ከእድሜ መጨመር ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመገጣጠሚያ አካላት በሽታ ይከላከላል፤
- በሎሚ ውስጥ ያለው ፔክቲን ፋይበር የመጥፎውን ኮልስትሮል መጠን ከመቀነሱም በላይ የመጥገብ ስሜትን ስለሚፈጥር በብዛት ከመመገብ ያግዳል፡፡

## 3. ሃባብ

- ለሰውነት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ቪታሚኖችን፣ ማዕድንና ሳይበዛ ለሰውነት በሚያስፈልግ መጠን ካሎሪንም የያዘ ተወዳጅ ፍራፍሬ ነው፤
- ውፍረት ለመቀነስ ይረዳል፤
- የስኳር በሽታን እና የልብ ህመምን ለመቆጣጠር ይረዳል፤
- ለሰውነት ተጨማሪ ኃይል ይሰጣል፤
- ለጤናማ የጸጉር እድገት ይጠቅማል፤
- ለጤናማ የምግብ መፈጨት ስርዓት እና የሰውነት ድርቀትን ለመከላከል ይረዳል፤
- ደም ግፊትን ይከላከላል፤
- ከጉልበት በታች የሚከሰትን ከፍተኛ የሆነ የደም ዝውውር ወይም ግፊትን ያስወግዳል፤
- ሰውነት ላይ የሚፈጠሩ አላስፈላጊ ነገሮችን ለማስወገድ በሚረዱ የቪታሚን ሲ አይነቶች የበለጸገው ሃባብ የካንሰር ተጋላጭነትን ይቀንሳል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# በሞባይል እዳ ውስጥ የተዘፈቁ ንሥሮችን ተከታይ አጥኚዎች

ከአገር አገር የሚሰደዱ ንሥሮችን እየተከተሉ የሚያጠኑ ሩሲያዊያን ሳይንቲስቶች ወደ ኢራንና ፓኪስታን ተጉዘው ገንዘባቸውን ከመጨረሳቸው በተጨማሪ በሞባይል የኢንተርኔት አገልግሎት ከፍተኛ እዳ ውስጥ ገብተዋል።

አጥኚዎቹን ለእዳ የዳረጓቸው ንሥሮች ከደቡባዊ ሩሲያና ከካዛኪስታን የተነሱ ሲሆኑ በተለይ ሚን ተብሎ የሚጠራው ንሥር ከካዛኪስታን ተነስቶ ወደ ኢራን ስለሚጓዝ እሱን መከተሉ ነው ለአጥኚዎቹ እዳ መናር ምክንያት የሆነው።

አጥኚዎቹ ከሚከታተሏቸው አእዋፋት ላይ የሚሰበስቡት አጭር የጽሑፍ መልዕክት እንዳሉበት አገር የክፍያ ተመን ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ ንሥሮቹ በሚሄዱባቸው አገራት ብዛት ክፍያው ከፍ እያለ ይሄዳል።

ሳይንቲስቶቹ የዱር እንስሳት ጥበቃን በተመለከተ ጥናት የሚያደርግ ሩሲያ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ማዕከል የበጎ ፈቃድ ተሳታፊዎች ናቸው።

አጥኚዎቹ የገቡበትን ችግር የተገነዘበው የሩሲያው የሞባይል ስልክ አገልግሎት አቅራቢ ሜጋፎን የተባለው ድርጅት እዳቸውን ሰርዞ ከዚህ በኋላ የሚጠቀሙትን የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት በቅናሽ እንዲከፍሉ ወስኗል።

ሳይንቲስቶቹ የገቡበትን የስልክ ዕዳ ለመክፈል በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያሉ ተከታዮቻቸው ገንዘብ እንዲለግሷቸው ጠይቀው ነበር።

አጥኚዎቹ በሞባይል የኢንተርኔት አገልግሎት እዳ ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ በማህበራዊ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



# ቦርሳ ውስጥ የተገኙ 20 ወፎች





ወፎቹ በትናንሽ ካርቶናች ውስጥ ነበር በዚህ መልክ የታሸጉት

ቤልጂየማዊው ተጓዥ በፔሩ ዋና ከተማ በሚገኘው ሊማ አየር ማረፊያ በእጅ ሻንጣው 20 ወፎችን ደብቆ ከሃገር ሊወጣ ሲል በቁጥጥር ሥር ውሏል።

ሂዮጉ ኮኒንግስ የተባለው የ54 ዓመቱ ጎልማሳ ወፎቹን በትናንሽ ካርቶኖች ውስጥ ካደረገ በኋላ ወደ ማድሪድ ስፔን ወስዶ ለመሸጥ አስቦ ነበር። ወፎቹን የወሰዳቸው ጥበቃ ከሚደረግላቸው የላቲን አሜሪካ ብርቅዬ አእዋፋት መጠለያ ነው።

ወፎቹ በታሸጉበት ካርቶን ውስጥ በሕይወት ቢገኙም ለሰዓታት በመቆየታቸው ላባቸው መርገፉን እና ፈሳሽ ከውስጣቸው የመመናመን ምልክት ማሳየታቸውን ባለሥልጣናት አስታውቀዋል።

በቁጥጥር ሥር የዋለው ቤልጂየማዊ «አእዋፋትን በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር» በሚል ክስ ተመስርቶበት የአምስት ዓመት እስራት ተፈርዶበታል፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ወፎቹ በፔሩ፣ በኢኳዶር እና በቦሊቪያ ጥቅጥቅ ደን ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ብርቅዬ የሆኑ አእዋፋት በብዛት በሚገኙባት በፔሩ ሕገ-ወጥ የዱር እንስሳት አዘዋዋሪዎች ስጋቷ ናቸው፡፡

# በሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተው የነበሩ 149 ግብር ከፋዮች

## 1. የሰሜን ምእራብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች

| No. | TIN | የግብር ከፋይ ስም |
|---|---|---|
| 1 | 0043885220 | A H M M TRADING P.L.C |
| 2 | 0020495319 | ABDULAHI EGG.MILK & MILK PRODUCTION MINI MARK. PLC |
| 3 | 0000238023 | ABOL BUNA PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 4 | 0046418002 | ADDIS MIRAPHE CONSTRUCTION MACHINERY RENTAL PLC |
| 5 | 0051944987 | AKBER INDUSTRY PLC |
| 6 | 0059498714 | AL ETFAQ TRANINIG CENTER |
| 7 | 0057085587 | AL NM TRADING PLC |
| 8 | 0049797078 | ALBATROSS BUSINESS PLC |
| 9 | 0057750350 | ALERT EXPRESS TRADING P L C |
| 10 | 0053236517 | ALFETIH ZIMO TRADING P L C |
| 11 | 0058042999 | ALNURSHEMSE TRADING PLC |
| 12 | 0047263088 | ALUMINA BUILDING CONSTRACTION CONTRACTOR PLC |
| 13 | 0046482949 | ANGETE MINING EXTRACTION PLC |
| 14 | 0003068272 | ARESEMA SALT PRODUCER PLC |
| 15 | 0045347172 | AS AS A CONSTRCTION PLC |
| 16 | 0040436770 | ASETANE WHOLESALES AND RETAIL TRADE PLC |
| 17 | 0040216656 | AUXIRE TRADING PLC |
| 18 | 0059231654 | BATA PRINTING ADVERT PLC |
| 19 | 0046004840 | BEG CASE DRINKS DISTRIBUTER SHARE COMPANY |
| 20 | 0045513979 | BENCH MARK ENGINERING PLC |
| 21 | 0004370093 | BEREH MOUNTAIN AGRO INDUSTRY P.L.C. |
| 22 | 0051163952 | BETE GEBREAL WOOD&METAL WORK S C |
| 23 | 0005161423 | BEZABEH AND MEKONNEN GENERAL TRADING PLC |
| 24 | 0005361585 | BIENVENIDO HOTEL AND BUSINESS TRAIDING PLC |
| 25 | 0005703813 | BILEN SECURITY AND SANITATION SERVICE PLC |
| 26 | 0052349279 | BK ARCHITECT ENGINEERING AND CONSULTANT PLC |
| 27 | 0055541242 | BOKRI SOFTWARE DEVELOPMENT P L C |
| 28 | 0002950986 | BRAND NEW TECHNIC VOCTIONAL TRANING PLC |
| 29 | 0049983454 | BRAWUN YEDORO ERBATA PLC |
| 30 | 0017127259 | CANCON CONSTRUCTION P.L.C |
| 31 | 0046715316 | CHEBELE TRADING PLC |
| 32 | 0037359844 | CINCOM COMMERCIAL PROJECTS P.L.C |
| 33 | 0000956206 | creative film production plc |
| 34 | 0058008788 | CWC CANVAS SHOES MANUFACTURING PLC |
| 35 | 0027239908 | D.M FARM PLC |
| 36 | 0041360675 | DA AD STEEL MANUFACTURING AND ENGINEERING PLC |
| 37 | 0049871362 | DAF GENERAL WATER WORKS CONSTRUCTION PLC |
| 38 | 0043648579 | DEGOS TRADING PLC |
| 39 | 0022713139 | DERTOGADA TRADING PLC |
| 40 | 0000146997 | DUKI PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 41 | 0002221657 | EBZOW CONSTRUCTION PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 42 | 0059271465 | ELEMAT TRADING PLC |
| 43 | 0061037468 | ERUGA TRADING PLC |
| 44 | 0054813435 | ESKAYFLAY TURE AND TRAVEL PLC |
| 45 | 0053092991 | ETHIOLOZA PRINTING AND ADVERTIZING P.L.C |
| 46 | 0000055836 | ETHIO-SEWERAGE SERVICE & IMPORT & EXPORT P.L.C. |
| 47 | 0042140599 | EXTRA ENGINEERING PLC |
| 48 | 0399086907 | EZERA AND HENOK CONSTRUCTION MACHINERY RENTAL PLC |
| 49 | 0000010878 | FAMILY TRADING PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 50 | 0000017290 | FETAN DEPARTMENT STORE PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 51 | 0005687397 | FIDEL INTEGRATED AGRO INDUSTRY PLC |
| 52 | 0001910887 | FRENCH DUCK FARM PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 53 | 0025246138 | FURKAN KINDERGARTEN SCHOOL SHARE CAMPANY |
| 54 | 0031272793 | G M T Z INTERNATIONAL TRADING PLC |
| 55 | 0060184586 | GAFAT MEDIA AND COMMUNICATIONS P L C |
| 56 | 0030197926 | GANZI MINING P.L.C |
| 57 | 0037366040 | GAPSWAP CONSULTANCY P.L.C |
| 58 | 0005041238 | GIMJABET PRESS WORKS PLC |
| 59 | 0043767819 | GREYMATTER CONSTRUCTION PLC |
| 60 | 0004941201 | GUREYGE GENERAL BUSINESS PLC |
| 61 | 0037575034 | H A F TOOLS GENERAL TRADING PLC |
| 62 | 0061198976 | H F SMART TRADING P L C |
| 63 | 0041351016 | H TT GG S TRADING PLC |
| 64 | 0047013871 | HAYTED CAF AND RESTAURANT PLC |
| 65 | 0050308214 | HELLBUHAN TRADING PLC |
| 66 | 0057177328 | ICARE ETHIO MEDICAL SOFTWARE PLC |
| 67 | 0045000914 | ICON DIGITAL PRESS P L C |
| 68 | 0003317669 | INTERFACING ETIOPIA COMPUTEK |
| 69 | 0043255620 | JETO PHARMACEUTICAL AND MEDICAL |
| 70 | 0060745562 | JULUN PLASTICS MANUFACTURING PLC |
| 71 | 0046748706 | K C C CONSTRUCTION PLC |
| 72 | 0041848363 | K F PLASTIC RECYLING FACTORY PLC |
| 73 | 0052377202 | K.L.B TRADING P.L.C |
| 74 | 0039623310 | KAMIL NURI BUSINESS PLC |
| 75 | 0058248694 | KARA GUDINA MODERN HOTEL&RECREATION PLC |
| [illegible] | [illegible] | [illegible] |
| 77 | 0007789147 | KENDA SEFER REAL ESTATE SHARE COMPANY |
| 78 | 0026392877 | KEYLINE GENERAL PRINTING AND ADVERTISING WOR |
| 79 | 0049950115 | LATIS CONSTRUCTION PLC |
| 80 | 0059862605 | LYRA TRADING PLC |
| 81 | 0040882855 | M A H A CONSULTING ENGINEERS PLC |
| 82 | 0041255376 | M A S TRADING PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 83 | 0026780662 | M D B GENERAL TRADING PLC |
| 84 | 0052766632 | M S N A TRADING PLC |
| 85 | 0005285402 | M.T.T GENERAL TRADING PLC |
| 86 | 0052360525 | MESTEFSHE KULU YE HITMET ENA MASETAWOQIYA SERA |
| 87 | 0043655635 | MILTO REALSTATE PLC |
| 88 | 0000010189 | MOLA MARU LIQUOR FACTORY PRIVATE LIMITED COM |
| 89 | 0023668210 | MUHIB PLASTIC PRODUCT FACTORY P.L.C |
| 90 | 0003406640 | MUKUER SALT MANFACTURING PLC |
| 91 | 0045661692 | MUYABU ELECTRIC AND BUILUDING MATERIAL GEN.TR.PLC |
| 92 | 0005739421 | NAHILA DRIVERS & OPRATERS TRAINING P.L.C |
| 93 | 0004240753 | NAMOY TRANSPORT PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 94 | 0022637357 | NAVID TRADING PLC |
| 95 | 0051687589 | NO MKAT TEREDING PLC |
| 96 | 0026932350 | NONAS GENERAL TRADING P.L.C |
| 97 | 0020493530 | NUTOL BUSINESS PLC |
| 98 | 0036634437 | NUTRAFRICA AGRO INDUSTRY & FOOD PROCESSING PLC |
| 99 | 0024285330 | OROMIA PAPERS MANUFACTURING P.L.C |
| 100 | 0015407017 | PEACOCK D.B APPLICATION GRAPHICS MEDIA CENTER P.LC |
| 101 | 0051491050 | PERPENGO TRADING P L C |
| 102 | 0050518112 | PHARMA VILLAGE PLC |
| 103 | 0038578439 | POLISHE CONSTRUCTION P.L.C |
| 104 | 0050853313 | POYAT GRAVEL CRASHER AND SALES P L C |
| 105 | 0046358918 | PULITZER MEDIA AND COMMUNICATION P.L.C |
| 106 | 0004707482 | R.S.H.R IMPORT PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 107 | 0056258783 | S A S B HOTEL PLC |
| 108 | 0038003807 | S P INDUSTRIAL PLC |
| 109 | 0037236583 | S.H.B INDUSTRY AND TRADE PLC |
| 110 | 0055320466 | SANSUZY TRADING PLC |
| 111 | 0046464777 | SATELAYT SECURITY AND CLEANING SERVICE P.L.C |
| 112 | 0049060082 | SAWUMET TRADING PLC |
| 113 | 0057624952 | SEBTENA TRADING PLC |
| 114 | 0047404189 | SEECHKO TRADING P L C |
| 115 | 0022319283 | SIGN GENERAL TRADING PLC |
| 116 | 0047047660 | SMART SECURITY AND HUMAN RESOURCE SERVICE P.L.C |
| 117 | 0025056182 | SOLBERG CONSTRUCTION P.L.C. |
| 118 | 0043086093 | SOLENET ACADEMY PLC |
| 119 | 0048785395 | SOLI COMMISSION AGENT PLC |
| 120 | 0003324541 | T.B.W TRADING PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 121 | 0005455597 | TAHSEBE BUSINESS S.C |
| 122 | 0045510436 | TAMUNE TRADING PLC |
| 123 | 0031070945 | TELEMED MEDICAL SERVICES P.L.C |
| 124 | 0059072843 | TG MA GARMENT PLC |
| 125 | 0001930426 | TRINITY ENTERPRISE PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 126 | 0000264143 | TSEHAY & MEKONNEN PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 127 | 0049167572 | UNITED BEVERAGE DISTRIBUTOR P.L.C |
| 128 | 0052187614 | WHOLE FUDS TRADING P L C |
| 129 | 0041734970 | Y A T KINDER AND PRIMARY SCHOOL PLC |
| 130 | 0051464493 | Y N Y TRADING PLC |
| 131 | 0041716451 | YABASIRE CONSTRUCTION WORK PLC |
| 132 | 0056832876 | YAWINDEW HOTEL SERVICE P L C |
| 133 | 0043262373 | YEFAM SOLAR ENERGY PLC |
| 134 | 0037904422 | YEMEA BAR AND RESTAURANT P.L.C |
| 135 | 0050133059 | YESHIMAC VEHICLES AND SPARE PARTS IMPORTER PLC |
| 136 | 0007066728 | YISTMA TRADE & INDUSTRY P.L.C |
| 137 | 0005516591 | YOMIF TRADING PLC |
| 138 | 0051248479 | YONIRUTH TRADING PLC |
| 139 | 0050432947 | Z MIKAEL PLC |
| 140 | 0052271888 | ZAEGOL TRADING P L C |
| 141 | 0007062087 | ZEGNU GENERAL TRADING PLC |
| 142 | 0003871179 | ZEWDENESH TRADING PRIVATE LIMITED COMPANY |

## 2. የሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች

| ተ.ቁ | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | የግብር ከፋይ ስም |
|---|---|---|
| 1 | 0003857607 | N+R ROOTS TRADING PLC |
| 2 | 0055884814 | ACCEL URBAN PLANNING AND RALATED CONSULTANCY PLC |
| 3 | 0057566268 | ADMAS MANUFACTURE OF BAKERY PRODUCTES PLC |
| 4 | 0000047893 | HONDAWA SHEKO ESHET BUNA PULPING PRIVATE LIMITED COMPANY |
| 5 | 0042937102 | SYDNY DRIVING LICENSE INSTITUTE PLC |
| 6 | 0045276495 | ASHOASHELA TAILOR PLC |
| 7 | 0051910322 | HASET CONSTRUCTION LIMITED COMPANY |





# ተቋማቱ የ52.2 ሚሊየን ብር ዕርዳታ ለገሱ

የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ለሜቄዶኒያ የአረጋዊያን የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማእከል እና ለባቡል ኸይር በጎ አድራጎት ድርጅት ከ52.2 ሚሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የቁሳቁስ ድጋፍ አደረጉ፡፡

በገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ እና በጉምሩክ ኮሚሽን አቶ ደበሌ ቃበታ የተለገሱት ዕርዳታዎች ለመቄዶንያ የ31.2 ሚሊዮን ብር እና ለባቡል ኸይር ከ21 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ምግብ እና መጠጥ እንዲሁም አልባሳት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

ሚኒስትሯ በዚሁ ጊዜ፤ ባለፉት አራት ዓመታት ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ኢኮኖሚያዊ ችግር ያለባቸውን ወገኖች የማገዝ ተግባር በመንግሥትም ትኩረት ተደርጎበት እየተሠራ ነው ብለው ይኸኛውም የዚያ አካል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ አቅመ ደካሞችን በመርዳት እያደረጉ ያለውን በጎ ተግባር አድንቀው ድጋፉ ወደፊትም እንደሚቀጥል ቃል ገብተዋል፡፡

የመቄዶኒያው መስራች አቶ ብንያም በለጠ እና የባቡል ኸይር መስራቿ ወ/ሮ ሀናን መሀመድ፤ የተለገሳቸውን ዕርዳታ በቀጥታ እንደሚያደርሱ አስታውቀው ድጋፉ በቀጣይም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል፡፡



# የኮንትሮባንዱ ሰንሰለት...

ከገጽ 8 የዞረ

በመመልመል ኮንትሮባንዱ ማለፉ የማይቀር በመሆኑ ጉዳዩን ለበላይ አመራር በማሳወቅ በጥልቀት ለመነጋገር የሥራ ሂደት አስተባባሪው ዋና ሳጅን አሜንን ወደ ቢሮ በመጥራት ውይይት አድርገዋል፡፡ በዚህም የሌብነት ሰንሰለቱንና በጉዳዩ የሚያገኘውን ጥቅም በመወያየት ስለሥራው አጠቃላይ ሁኔታ በሌላ ጊዜና በሌላ ቦታ በመገናኘት እንደሚያወሩ በመቀጣጠር ተለያዩ፡፡

ጥር 2/2013 ዓ.ም. አዋሽ ሰባት ኪሎ አቢሲኒያ ሆቴል ዋና ሳጅኑ የሥራ ሂደት አስተባባሪውንና ኮንትሮባንዲስቱን አገናኛቸው፡፡ በዚህም መሰረት ኮንትሮባንዲስቱ ደሳለኝ የሥራ ሁኔታው በንግድ ሥራ የተሰማራ ሲሆን ከዚህ ቀደም የስርቆት ሰንሰለት በማዘጋጀት ዕቃ ሲያሳልፍ የነበረ ነው። ለአብነትም መስከረም 27/2013 ዓ.ም. ከምሽቱ 4፡00 ድንበር ተሻጋሪ በሆነ መኪና በታርጋ ቁጥር ኢት. 3-83764/24467 በዕለቱ በነበረ ፈታሽ ሁሴን መሀመድ አብዱ ተፈትሾ መኪናውን ባዶ በማስመሰል ሊያልፍ ሲሞክር በድንገተኛ ፍተሻ ተፈትሾ የ459ሺ ብር ዕቃ ተይዞበት ነበር፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሀሰተኛ የጉምሩክ ሰነድ በማዘጋጀት ሊያልፍ ሲሞክር ተደርሶበት ኬላውን በኃይል ጥሶ እንደሄደ እና ለዚህም የፌደራል ፖሊሶች ከለላ እንደሰጡት ለማስረዳት ሞክሯል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሀሰተኛ የመንገድ ወረቀት በማዘጋጀት አምስት ጊዜ፤ ያለሰነድ ደግሞ 21 ጊዜ ማሳለፍ እንደቻለ አስረድቷል፡፡ ይህንን ሲሠራም ነባር የጉምሩክ ሠራተኛ እንዳለውና ፈቃደኛ ከሆነ ከአዲሱ ሰንሰለት ጋር እንደሚያስተዋውቀው በመግለጽ የሥራ ሂደት አስተባባሪውን ለማስረዳት ይሞክራል፡፡

ለአዲሱ የኮንትሮባንድ ሰንሰለት የፍተሻ ባለሙያው አቶ ሁሴን መሀመድና ም/ኢንስፔክተር አብዲ ሸይቼ አባላት መሆናቸውን ዋና ሳጅኑ ለአቶ ካሳሁን እምሩ የማስተዋወቅ ሥራ ሠርቷል፡፡ በዚህም መሰረት ኮንትሮባንዲስቱ በአንድ ኮንቴነር 200ሺ ብር ሊከፍል የተስማማ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 50ሺ ለአቶ ካሳሁን እንዲሰጠው ተወስኗል፡፡

የኮንትሮባንድ ዕቃው ከመምጣቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የካቲት 30/2013 ዓ.ም. በአዋሽ ሰባት ኪሎ ሩት ቪሌጅ በመገናኘት ባደረጉት ውይይት ዕቃው ከገዳማይቱ ተነስቶ በፍተሻ ባለሙያው ሁሴን መሀመድ አማካኝነት እንደተፈተሸ በማስመሰል አስፈላጊ መረጃ ሞልቶ እንዲለቀው ነው የተወጠነው፡፡ የፌደራል ፖሊስ የሻለቃው አስተዳደር ኢንስፔክተር አየለ ለማ የኮንትሮባንድ ሰንሰለት ዋና መልማይ እንደሆነ እና አቶ ደሳለኝ ገብረክርስቶስ ስለ ዕቃው ዝርዝር መረጃዎችን የካቲት 28/2013 ዓ.ም. ለአቶ ካሳሁን እምሩ እንዲደርሰው ተደርጓል፡፡

መጋቢት 1/2013 ዓ.ም. ጠዋት 3፡00 አካባቢ በመሀመድ አብዱል ከሪም አሽከርካሪነት ዕቃው አዋሽ ኬላ የደረሰ ሲሆን በዕለቱ በነበረ ፈታሽ ሁሴን መሀመድ አማካኝነት ጭነቱ ሕጋዊ እንደሆነ በማስመሰል፣ ሀሰተኛ የትራንዚት ቁጥር በመሙላት እና ማህተም በመምታት እንዲለቀቅ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አቶ ደሳለኝ መጋቢት 2/2013 ዓ.ም. ለሌብነት ሰንሰለቱ እንዲያከፋፍል 200ሺ ብር የሰጠው ሲሆን በዚህ ሰንሰለት የተሳተፉ ሰባት አባላት በመሆናቸው እኩል ሲካፈሉ 28ሺ 571.43 ብር እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ አቶ ሁሴን መሀመድም ከአቶ ካሳሁን እጅ 28ሺ 600 እንዲቀበል ተደርጓል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ካሳሁንን ጨምሮ ሦስት የኮሚሽኑ ሠራተኞች በማኔጅመንቱ እውቅና መሰረት እየተወኑ በመሆናቸው ሌሎች የኦፕሬሽን ሥራዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ 91ሺ 685 ብር በካሽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

የመጀመሪያው ዙር እደተጠናቀቀ የፌደራል ፖሊስ አባላት ማለትም ሻለቃው ባልታወቀ ምክንያት ወደ አልበረከቴ የተዛዋሩ ቢሆንም ኢንስፔክተር አየለ ለማ ጥቅሙን ለማስከበር ከዋና ኮንትሮባንዲስቱ አቶ ደሳለኝ ጋር መጋቢት 22/2013 ዓ.ም በአዋሽ 7 ኪሎ ሩት ቪሌጅ በመገናኘት ከዚህ በፊት ያለፈው የኮንትሮባንድ ዕቃ በተመለከተ ደካማና ጠንካራ ጎን ገምግመውና ሌሎች መረጃዎችን ተለዋውጠው ተለያዩ፡፡

መጋቢት 23/2013 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡20 አካባቢ በኮንቴነር ቁጥር TGBU 2394830 እና TCKU 3400819 በተሽከርካሪ ኢት. 3-83764/24467 የማሽጊያ ቁጥር EU 17403036 ወደ አዋሽ መፈተሻ ኬላ ደርሷል፡፡ እንደተለመደው በፍተሻ ሠራተኛው ሁሴን መሀመድ አማካኝነት ጭነቱን ሕጋዊ በማስመሰል እና በዕለቱ በስሙ የተመዘገበውን ማህተም በመምታት ኬላውን እንዲያልፍ ተደረገ፡፡ ከዚያም እቃው በጉዞ ላይ እንዳለ ወደ 10፡20 ገደማ መተሀራ ከተማ ህይወት ሆቴል ውስጥ ካሳሁን እምሩ፣ ኢንስፔክተር አየለ ለማ እና ደሳለኝ ገብረ ክርስቶስ በመገናኘት ተወያይተዋል፡፡ ምክትል ኢንስፔክተር አብዲ ሸይቼ እና ዋና ሳጅን አሜ ኢስማኤል ስለ ኮንትሮባንዱ ስለሚያውቁ አቶ ደሳለኝ ከ200ሺ በተጨማሪ 10ሺ እና ከዋናው 10ሺ ባጠቃላይ 20ሺ እንዲሰጥ ተስማምተዋል፡፡ በተጨማሪም ከኢስፔክተር አየለ ለማ ጋር ለሚሠሩ ተጨማሪ ሰዎች 40ሺ ቢጠይቅም 35ሺ እንዲበቃው ተስማምተዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሰንሰለቱ የተካተቱ ሰዎችን እጅ ከፈንጅ ለመያዝ ከፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ የተውጣጣ ግብረ-ኃይል እንዲሁም የኮሚሽኑ ሠራተኞች በገንዘብ ክፍፍሉ ወቅት እንዲያዙ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህ ወቅት የመተሃራ ፖሊስ አዛዥ ለዋና ኮንትሮባንዲስቱ ሽፋን በማድረግ በመርማሪ ፖሊሱ እና በኮሚሽኑ የኢንተለጀንስ ባለሙያ ላይ የግድያ ሙከራ ቢያደርግም በፌደራል ፖሊስ ግብረ-ኃይል በቁጥጥር ስር ሊውሉ ችለዋል፡፡ ዕቃውን የጫነው መኪናም በደረሰበት በሌላ ግብረ-ኃይል ክትትል ሲደረግበት ቆይቶ ከነሾፌሩ ተይዟል፡፡ የፍተሻ ባለሙያው ሁሴን እንደለመደው ከአቶ ካሳሁን እምሩ ሊቀበል አዋሽ ሩት ቪሌጅ ተገናኝተው ሲቀበል ለመያዝ ቢሞከርም ጊዜው ምሽት በመሆኑ ገንዘቡን እንደተቀበለ ሊያመልጥ ችሏል፡፡

ይህን ጉዳይ የተከታተለው የልደታ ምድብ ችሎት ወንጀለኞችን እንደየተሳትፏቸው ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

**ምንጭ፡-** የጉምሩክ ኮሚሽን ኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት

# ኮሚሽኑ...

ከገጽ 1 የዞረ

የዓለም አቀፉን የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት የተከተለ የአገልግሎት ደረጃ ለማስፈን ደግሞ እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ እንሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡

የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ሮቤል ተስፋዬ፤ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ በርካታ ተቋማትን ወደ ሥርዓቱ በማስገባት ደንበኞች የጊዜ፣ የገንዘብ እና የድካም ጫናቸው እንዲቃለልላቸው መደረጉን አመልተዋል፡፡ እነዚህ ሦስት ተቋማትም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸው ለራሳቸው እና ለደንበኞቻቸው የሚሰጠው ጠቀሜታ የጎላ እንደሆ ጠቁመዋል፡፡

ስምምነቱን ከኮሚሽኑ ጋር የተፈራረሙት ተቋማት ኃላፊዎች ደግሞ አጠቃላይ የንግድና የሎጂስቲክ ስርዓቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማገዝ እየተደረገ ያለውን ጥረት አድንቀው ኮሚሽኑም ሆነ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወደዚህ ሥርዓት መግባታቸው የሚሰጡት አገልግሎቶች ከብልሹ አሠራር እና ከሙስና ፀድተው ምቹ የአሠራር ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

# ሕግ-ግብር

ይህ አምድ የታክስ አስተዳደርና የጉምሩክ አሠራር የሚመራበትን ህጐች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች፣ ለሕግ ተገዢነት የሚያስተምሩ አስተሳሰቦችን፣ ሕጎችን ለአሠራር ምቹ የሚያደርጉና ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያጎለብቱ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅ ጽሑፍ ይቀርብበታል፡







## ሀሰተኛ ደረሰኝ ሲያትሙ እና ሲያሰራጩ የተደረሰባቸው ተያዙ

በገቢዎች ሚኒስቴር የአዳማ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በከተማዋ በ35 ድርጅቶች ስም ሀሰተኛ ደረሰኝ በማተም እና በማሰራጨት ሕገ-ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን አስታወቀ፡፡

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን ደርቤ እንደገለጹት፤ ግለሰቦቹ የተያዙት በከተማዋ ፈቃድ አውጥተው በተሰማሩ ሕጋዊ ድርጅቶችና እና ሆቴሎች የንግድ ስም በመጠቀም ግብይት ባልተፈፀመበት እንደተፈፀመ አስመስለው ሀሰተኛ ደረሰኝ በማተም እና በመሸጥ ላይ ስለተሰማሩ ነው፡፡

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለሁለት ወራት በተደረገ ክትትል በሕጋዊ ድርጅቶቹ ስም የታተሙ ሀሰተኛ ደረሰኞች እና ዋነኛ የድርጊቱ ተጠርጣሪዎች እጅ ከፍንጅ ተይዘዋል፡፡ በዚህም መሠረት ደራ ማተሚያ ቤት በሚል የድርጅት ስም ሕገ-ወጥ ደረሰኞችን እና ሌሎች ሰነዶችን ሲያዘጋጅ እና ሲያሰራጭ የነበረ ግለሰብ ከነግብረ-አበሮቹ በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

የወንጀሉ ፈጻሚዎች መሰብሰብ ያለበትን ግብር በመሰወርና ሀገር ልታገኝ የነበረውን ገቢ ከማሳጣት ባለፈ ኢኮኖሚው ላይ ቀውስ በመፍጠር በሀገር ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሲያደርሱ መቆየታቸውን ጠቁመዋል፡፡

ግለሰቦቹ በቁጥጥር ስር ሲውሉ ከደረሰኞቹ ህትመት እና ስርጭት ባለፈ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች፣ የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች ሰነዶችንም በማዘጋጀት ለደህንነት ስጋት የሚሆኑ ወንጀሎችን ሲሠሩ መቆየታቸው ተደርሶበታል፡፡

ወንጀሉ በስማቸው የተፈጸመባቸው የወሰን ማተሚያ ቤት እና የግሬስ ሆቴል ባለቤቶች በበኩላቸው፤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ባደረገው ክትትል ሕገ-ወጦቹን በቁጥጥር ስር ማዋሉ በድርጅታቸው ላይ ሊደርስ የነበረውን ተጨማሪ ኪሳራ ማስቀረቱን አንስተዋል፡፡ በመሆኑም ወንጀሉ የሀገር ክህደት ጭምር በመሆኑ አስተማሪ ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡




## የተበጠሰው የኮንትሮባንዱ ሰንሰለት


ታህሳስ 19/2013 ዓ.ም. ከቀኑ 4፡00 አካባቢ የፀረ-ኮንትሮባንድ ግብረ ኃይል አባል የሆነው ዋና ሳጅን አሜ እስማኤል ሙሳ በወቅቱ የአዋሽ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር የሥራ ሂደት አስተባባሪ ካሳሁን እምሩ ቢሮ ይገባል፡፡ ከዚያም በሌብነት ሰንሰለት የኮንትሮባንድ ዕቃ እንዲያሳልፍ የድርድር ጥያቄ ያቀርብለታል፡፡ ጉዳዩን ሊፈትነው ያመጣው ወይም ሕገ-ወጥነቱን በጋራ በመሥራት ጥቅሙን ለመካፈል እንደሆነ በመጠርጠር ጉዳዩን ለማጤን ጊዜ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል፡፡

አቶ ካሳሁን ያጋጠመውን ነገር ለቅርብ ኃላፊው የሕግ ተገዥነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ለአቶ ዘላለም ክንፈ በመንገር የድርድር ጥያቄውን እንዲቀበል ተወሰነ፡፡ ምክንያቶቹም፤ የድርድር ጥያቄ ያቀረበው አካል ሰንሰለቱ እሰከምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ እና የኮንትሮባንድ አሠራሩ በምን ዓይነት ሁኔታ ኬላውን እንደሚያልፍ ተገንዝቦ ትምህርት ለመውሰድ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የኮንትሮባንድ ዕቃው መነሻውንና መድረሻውን ለማጣራት እና የኮንትሮባንድ ዕቃውን ባለቤት ለመለየት ነው፡፡

በሌላ መልኩ የሥራ ሒደት አስተባባሪው ድርድሩን ባይቀበልም ሌሎች የተቋሙን ሠራተኞች

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

በ8199 ነጻ የስልክ ጥሪ ማንኛውንም መረጃ እና ለጥያቄዎቻችሁ ምላሽ ስለሚገኝበት በመደወል እንድትጠቀሙ እናሳስባለን።




በታክስ እና በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለማግኘት 8199

**የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ**

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

**እ ሴ ቶ ች**

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)